## ለኹለተኛው የቀሲስ መብራቱ እ-ጦማር የተሰጠ መልስ፡-

"Miaphysite Christology –An Ethiopian Perspective" የሚለውን መጽሓፍዎን አነበብሁት። አንብቤ ከጨረስሁት፡ የቆየሁ ብኾንም፡ በጊዜው፡ ይህን ደብዳቤ ከመጻፍ እንዲህ የዘገየሁት፡ በቀደመ የሥራ ብዛት ምክንያት መኾኑን፡ ልገልጽ እወድዳለሁ።

ይኸው መጽሓፍዎ፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፡ በተለይ፡ ከግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አግኝታና ተቀብላ፥ እውቅና ሰጥታና አጽንታ ስትመራበት ስለቆየችው፥ ዛሬም፡ እየተከተለች ስላለው ሃይማኖት፥ እንዲሁም፡ ይኸው፡ ሃይማኖት፡ "ተዋሕዶ" ከሚለው፡ ከኢትዮጵያዊው የግእዝ ምሥጢራዊ ቃል ጋር ስለተያያዘበት የነገረ መለኮት ፍሬ ሓሳብና ትርጉም፡ ኢትዮጵያዊዉን አስተሳሰብና አመለካከት መሠረት በማድረግ፡ ሥርዓታዊ ጥናትን ያካኼዱበትና ሓተታዊ ትንተናን የሰጡበት በመኾኑ፡ የሚያረካና የሚደነቅ ኾኖ አግኝቼዋለሁ።

"የኢትዮጵያ ነው" ተብሎ የኖረውና አኹንም፡ በዚሁ መልኩ የቀጠለው፡ የቅብጥ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት፡ የተሳሳተ ዘይቤና ትርጓሜ እየተሰጠው፡ በወገን ኾነ በባዕዳን ዘንድ፡ ብርቱ ጠንቅን በማስከተሉ፡ ተከሥቶና ሥር ሰድዶ የቆየውን ረቂቅ ችግር ለማስወገድ፡ ይህ ሥራዎ እንደሚረዳ፥ ከዚህም ጋር፡ በዚህ ረገድ፡ በአገር ደረጃ ሳይቀር፡ ለሚካኼደው ተመሳሳይ ምርምር፡ ከፍተኛ ድጋፍና አስተዋጽኦ እንደሚኖረው አይጠረጠርም።

እርስዎም፡ በኢትዮጵያዊነትዎ፡ ለእናት አገርዎና ሃይማኖትዎ፡ ይህን ዓይነቱን የተልእኮ ግዳጅ፡ በበኩልዎ በመፈጸምዎ ደስ ሊልዎት ይገባል፤ ለበለጠ ጥረትም፡ ራስዎን ለማዘጋጀት የሚያበቃዎ ከመኾኑ ጋር፡ በዚህ ሃይማኖታዊ ምግባርዎ፡ ያስገኙት ይኸው ፍሬ፡ በመልካም አርአያነቱ፡ እንደቀዳሚዎቹ ኹሉ፡ ለሌሎችም፡ ጠቃሚ ኾኖ ይገኝ ዘንድ፡ ብሩህ ተስፋን እንደሚፈነጥቅ ይታመናል።

እንዲህ ከኾነ፥ ማለትም፡ ከአይሁድም ኾነ ከግብፃውያን፡ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው፡ የሃይማኖት ውርስ፡ ኢትዮጵያን፡ እንዲህ ላለው ጠንቅ ከዳረገ፥ የኹላችንም፡ የተልእኮ ዓላማ ደግሞ፡ እርሷን፡ ከዚህ ጠንቅ ማውጣት ከኾነ፡ ታዲያ! እኛ፡ ኹላችን፡ በዚህ ረገድ፡ ምን ማድረግ ይገባናል? ምንስ ይጠበቅብናል?

መልሱ፡ ቀጥታና ግልጽ፥ አጭርም ይመስለኛል፤ ይኸውም፡ ዘሩ፥ ግንዱና ፍሬው፡ "ቅዱሱ ኪዳን"፥ መገለጫውም፡ "ተዋሕዶ" የኾነውን፡ እውነተኛውንና ጥንታዊዉን፡ የኢትዮጵያን መለኮታዊ ሃይማኖት፡ በትክክልና በይፋ ማስታወቅ ነው። እርሱም፡ በቀዳማዊው፡ የኪዳነ ልቦና መሠረት ላይ የታነጸውና በማእከላዊው የኪዳነ ኦሪቱ አቋም ላይ በጸናው ግድግዳ አማካይነት፡ ለመጨረሻው የኪዳነ መንፈስ ቅዱስ ጉልላት የበቃው፡ ኢትዮጵያዊው የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት ነው።

አዎን! "የእግዚአብሔር ልጆች" በተባሉት፡ በኢትዮጵያውያኑና በኢትዮጵያውያቱ፡ በእነኖኅና በእነመልከ ጼዴቅ፥ በእነዮቶርና በእነንግሥተ ሳባ፥

በመጨረሻም፡ በድንግል ማርያምና በልጇ በኢየሱስ ክርስቶስ፥ ከዚያም፡ "አቤሜሌክ" በተባለው፡ በአዲስ ኪዳኑ ጃንደረባና በእነንግሥት ሕንደኬ፥ ቀጥሎም፡ በአኵሱሙ ሊቀ ካህናት በእነእንበረምና በእነቅዱስ ያሬድ ተጠብቆ የኖረው፥ ዛሬም፡ በእውነተኞቹ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ ጸንቶ የሚገኘው ሃይማኖት ነው።

አዎን! ከአዳምና ሔዋን አንሥቶ፡ በእኒያ ቅዱሳንና ቅዱሳት አማካይነት ሲያያዝ፡ ከእኛ የደረሰው፥ ከአይሁድ ኦሪትና ከሓዋርያት ብሥራት፥ ከብሉዩና ከሓዲሱ ኪዳናት ሊቃውንት መጻሕፍትም በፊት የነበረው፥ የሰባት ሺ አምስት መቶ አራት ዓመታት ዕድሜ ያለው፡ መለኮታዊው የኢትዮጵያ ሃይማኖት ነው።

ታዲያ! ይህ ሃይማኖት፡ የጥናትዎና የምርምርዎ መደምደሚያ ኾኖ፡ በመጽሓፍዎ መጨረሻ ላይ፡ ሊቀርብ ይገባ፥ ያስፈልግም የነበረ አይመስልዎትምን?

ይህ ኢትዮጵያዊ ሃይማኖት፡ ያስታውሱ እንደኾነ፡ ከእርስዎ ጋር፡ ቀደም ብለን ባደረግነው፡ የጎዋ ሰሌዳችን ደብዳቤ ልውውጥ ጊዜ፡ ከሌሎቹ ጋር፡ በጥናትዎና በምርምርዎ መካከል፡ ጣልቃ አስገብተው "ሊመለከቷቸው የተገቡ ናቸው!" ብዬ፡ ጠቅሼልዎ በነበሩት መጻሕፍቴ ውስጥ ታትሞ፡ ለይፋ ምንባብ የበቃው ሲኾን፡ አኹንም፡ እነሆ፡ ይህንኑ ሃይማኖታችንን፡ በጽሑፋዊ መግለጫ፡ ከዚህ ደብዳቤዬ ጋር፡ ዐባሪ አድርጌ ልኬልዎታለሁ።

አምላከ ኢትዮጵያ፡ በቅዱስ መንፈሱ ጸጋ፥ በቅድስት እናቱም ረድኤት፡ በየተልእኳችን፡ ለእርሱ የሚያስደስተውን፥ እኛም የሚገባንን መልካሙን ኹሉ ፈጽመን እንድንገኝ እንደሚያደርገን እናምናለን።

በቅዱሱ ኪዳን፡ የእግዚአብሔር መንግሥቷ ኢትዮጵያ አገልጋይ፤
ንቡረ-እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ።